# ሽል እንዳለ ቢቀር

የተዋህዶ ልጅ ፤ ልብ አድርገህ ስማ
በህልውናህ ላይ ፤ አንዣቧል ጨለማ
መናፍቅ ነው ያለው ፤ ከስልጣኑ ማማ
ላውሬው ሊያስረክባት ፤ ኦርቶዶክስ ተዳክማ
ውጊያው ተጀምሯል ፤ በሰንደቅ አላማ
በእምነትህ ፀንተህ ፤ ቅለጥ እንደሻማ
በእምነትህ ዋልታ ፤ በእምነትህ አውድማ
ሌጊዮን ሰልጥኗል ፤ ነፍስህን ሊቀማ ።

በፈጣሪ መንገድ ፤ የተራመዱትን
ጌታችን አክብሮ ፤ ከፍ ከፍ ያሉትን
ክብር የማይሰጡ ፤ ቤዛዊት እናትን
ፃድቃን ሰማዕታት ፤ አዛውንት አባትን
እንደተራ ነገር ፤ የሚያዋርዱትን
እኒህ ጉግ ማንጉጎች ፤ ባገር የፈሉትን
ለማየት የሚሹ ፤ የኦርቶዶክስ ሞትን
የአርዮስ ልጆች ፤ የእሳት አራትን
አጥብቀህ ተዋጋ ፤ ሳትፈራ ሞትን ።

ባዋጅ ተጀምሯል ፤ ግልፅ ጦርነቱ
ጫና ቢበረታም ፤ ቢከፋም ግፊቱ
አይለው ቢታዩ ፤ በኃይል በጉልበቱ
ሰቆቃው ቢበዛ ፤ ስቃይ እንግልቱ
ዛሬ ቢያሳድዱህ ፤ እረተው ላይረቱ
የግድ ነውና ፤ ሊፈፀም ትንቢቱ
በመከራ ዘመን ፤ ፍቱን መድሃኒቱ
አለመወላወል ፤ በእምነት በፀሎቱ ።

ቀድሞም የምናውቀው ፤ ተዋህዶ ገድሉ
ጌታ እንዳስተማረን ፤ እንደ እምነት ወንጌሉ
ሲናወጡ መፅናት ፤ ቢያይልም ማዕበሉ
የክብርም ክብር ነው ፤ ለእምነት መጋደሉ
ጦር መሳሪያ ሳይሆን ፤ ከሁሉም ኃያሉ
የኛ አሸናፊያችን ፤ ነውና መስቀሉ ።

ይሄ ክብር ዝና ፤ ከንቱ ሆኖ ሊቀር
ከአጋንንት ጎራ ፤ ይዟት ለመደመር
ፈተናን ሊያፀና ፤ የመጣብን ባገር
ቃል እያሳመረ ፤ አስውቦ የሚናገር
የበግ ለምድ ለባሽ ፤ የዲያቢሎስ ጨንገር
ትዕቢተኛ መሪ ፤ መቅደስ የሚዳፈር
ከፈጣሪው ጋራ ፤ ደፍሮ የሚገዳደር
ምነው እናቱ ሆድ ፤ ሽል እንዳለ ቢቀር ።

ታዛቢው

September 27, 2019